# ይድረስ ለጀርመን ድምፅ ያማርኛው አገልግሎት

ቦን/ጀርመን

በተቀዳሚ ስላምታችን ይድረሳችሁ።

ቀጥሎም እ.አ.አ በ23.03.2017 ዓ.ም የዜና መጽሔት ትንተናቹሁ አራት የኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ማለትም የኦሮሞ አቦ ግንባር፣ የኦሮሞ ነፃነት አንድነት ግንባር፣ የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ፣ የኦሮሞ ነፃነት ብሔራዊ ፓርቲ ከተሰኙት ሁለት ተወካዩች ቀርበው አዲስ አበባ ከተማን የኦሮሚያ ክልልና የአዲስ አበባ አስተዳደር በጋራ እንዲያስተዳድሩዋት እንዲሁም ባለፉት 25 ዓመታት ከከተማዋ የተፈናቀሉ የኦሮሞ ተወላጆች ካሣ እንዲክፈላቸው ጠይቀዋል።

ዳሩ ግን ያለ ኢትዩጵያ ሕዝብ ተሳትፎና ይሁንታ በወያኔ ትግሬ ሕወሐትና ተለጣፊዎች የተዘጋጀውን የባንቱስታን አፓርታይድ የጎሣ ፌደራሊዝምና ሕገ መንግሥት ተብዬው መሠረት የኦሮሚያ ክልል ከአዲስ አበባ ማግኘት የሚገባውን ልዩ ጥቅምና ባለቤትነት ለማስከበር፣ በአዲስ አበባ የኦሮሞን ባሕልና ቋንቋ ለማስፋፋት ማቀዳቸውን ተወያዩች ገልጸዋል።

እጅግ በጣም የአስገረመን ነገር ቢኖር አወያዩ ወይም ጠያቂው የጀርመን ድምፅ ጋዜጠኛ ከወረሞ ብሔረተኞች የተነገረውን እንዳለ እንደወረደ አናፈሰ እንጂ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ሕዝብ የማንም መጠቀሚያና ልዩ ሃብት ያለመሆኑን፤ ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብትና ነፃነት ያለው መሆኑን አላገናዘበም። ስለሆነም ነው ይህን ደብዳቤ ለመጻፍ የተገደድነው።

በግልጽ እንደሚታወቀው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ሕዝብ በቅጥረኛው ወያኔ ትግሬ አናሳ ጎሣና ተለጣፊዎቹ ኢዲሞክራሲያዊ አምባገነን የባንቱስታን አፓርታይድ የጎሣ ፖለቲካ ሰለባ ነው። ሕዝቡ ዲሞክራሲያዊና ሰብእዊ የሆነ ራሱን በራሱ በነፃነት የማስተዳደር መብትና ነፃነቱን ተገፏል። በመሆኑም የራሱን ከንቲባና አስተዳዳሪዎች በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመምረጥ አይችልም።
ይባስ ተብሎም በየጊዜው ከቤት ንብረቱ በወያኔ ወራሪ ታጣቂዎች እንበለ ፍትሕ ከየክፍለ ከተማው የሚፈናቀለው ሕዝብ ቁጥር እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው። በአንጻሩ ጥቂት ወያኔ ትግሬዎችና ግብረበላዎቻቸው በአዲስ አበባ ከተማ ሰፊ ሕዝብ ኪሣራ ሲንደላቀቁና በምቾት ቅንጦት ሲምነሸነሹ የአብዛኛው አዲስ አበቤ ኑሮ ከሞቱት በላይ፣ ከቁሙት በታች እንድሆነ የተረጋገጠ ነው።

የወያኔ ትግሬ ኢሕአዴግ ተብዬው ታማኝ ተቃዋሚዎች በአዲስ አበባ ተደንሽረው እየተሞዳሞዶ በአጃቢነት ይኖራሉ። ተቃዋሚዎች በነዋሪው ሕዝብ ላይ የሚፈጸመውን ከፍተኛ የአስተዳደር በደልና ግፍ፣ ዐይን ያወጣ ሃብት ንብረት ዝርፊያፉ፣ የባሕልና ቅርስ ማውደም፣ የነዋሪዎች መፈናቀል፣ ለኑሮ አስፈላጊ ግብአቶች አለማቅረብና ከፍተኛ የዋጋ ንረት ወዘተረፈ ሁሉ ለአስመሳይ ተቃዋሚዎች ሁሉ ምናቸውም አይደሉም። አዲስ አበባ ባለቤተየለሽ ከተደረገችበት ጀምሮ የወያኔዎች ተለጣፊዎቻውች መፈንጭያ ሆና ታጥራለች።
በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ እራሳቸውን የኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚሉት ጠባብ ጎሥኞች የአዲስ አበባን ሕዝብ የራስን በራስ ማስተዳደር ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብት ረግጠው ከተማዋ በኦሮሚያ ክልል ተብዬው ሥር እንድትሆን ይፈልጋሉ። አልፈው ተርፈውም ከአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ከመኖሪያቸው የተፈናቀሉ ኦሮሞዎች ዘር ማንዘራቸው ተፈልጎ ካሳ ይገባቸው ነበር እያሉ የሚያላዝኑት እነዚህ ፓርቲዎች አሁን ግን ቢያንስ በ25 ዓመቱ የኢሕአዴግ ዘመን ከከተማዋ የተፈናቀሉት ገበሬዎች ከያለበት ተሰብስበው ተገቢ ካሣ እንዲከፈላቸው ማሳሰባቸውን አሳውቀዋል።
ከዚሁ ጋራ በተያያዘ የናዝሬት ከተማ የምትገኝበትን ሁኔታ ማገናዘቡ ይጠቅማል። ናዝሬት የኦሮሚያ ክልል ተብዬው ዋና መዲና ናት ተብሏል።

ነገር ግን ከነዋሪዎቹዋ 75 በመቶ እጅ የሚሆኑት ዐማርኛ ተናጋሪዎች ቢሆኑም እንኳ ዐማሮች በራሳቸው ፊደልና ቋንቋ እንዳይጠቀሙ ተከልክለዋል፤ በግዳጅ ጥቁር ፈረንጅ እንዲሆኑ ተደርጎ በቁቢ ላቲን ፊደልና በኦሮምኛ ቋንቋ ማመልከቻ እንዲጽፉ ይገደዳሉ። በአጠቃላይ ከፖለቲካውና ኢኮኖሚው ዘርፍ የናዝሬት ከተማ ነዋሪ ዐማሮች በሁለተኛ ደረጃ ዜግነት የተገለሉ ናቸው። በሐረር ከተማም የዐማራውን ሕዝብ ቁጥር ከአደሬው ጋራ ሲነፃፀር በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ምክንያት ለማሳናስ ታስቦ ነው በሐረር ከተማ ዙሪያ ያሉት ከ20 በላይ የቀበሌ ገበሬዎች (ቆቱዎች) ከኦሮሚያ ክልል ተብየው ተወስደው የወያኔ ትግሬዎች ታማኝ ጉልት ዕቃ ለሆነው የሐረሬ ክልል የተደረቡት። በአንድ በኩል ክልል የተደረገው በቋንቋ መሥፈርት ነው እየተባለ ሲለፈፍ በሌላ በኩል ደግሞ ኩሻዊ ቆቱዎች ከአደሬ ሴማዊ ተብዬ ቋንቋ ቡድን ጋራ አብረው ተከልለዋል። እንዲሁም በሸዋ ስላሌ አውራጃ አባይ ወንዝ ዳርቻ እነ ጎሐ ጽዩን፣ ፍልቅልቅ፣ ዋሻ ሚካኤል፣ ግንደበረት፣ ወዘተረፈ ነባር ነዋሪው ሕዝብ ዐማርኛ ተናጋሪዎች የሆኑት ያለ ፍላጎታቸው የኦሮሚያ ክልል ተብዬው ሥር ተጠቃለው ልጆቻቸው በቋንቋቸው እንዳይማሩ ተደርገዋል።

የኦሮሞ ብሔረተኛ ተቃዋሚ ፓርቴዎች በአንድ በኩል ፊንፊኔ የኛ የብቻችን ናት እያሉ ይለፍፉሉ። በሌላ በኩል አዲስ አበባ ከተማ ወደጎን መስፋት የለባትም፣ ወደ ጎን ከሰፋችና በዙሪያ ካሉት ከተሞች ጋራ የተቀናጀ ዕቅድ ከአደረገች ይህ የዐማራ ባሕልና ቋንቋ ስለሚያስፋፍ እንፈቅድም እያሉ ቡራ ከረዩ ብለዋል። እነዚህ ተቃዋሚ ፓርቲ ተብዬዎች የአዲስ አበባ ከተማን ከስምንት ሚሊዎን በላይ ነዋሪ በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው የናዝሬትና ሌሎች ከተሞች ሕዝብን በግዳጅ ኦሮሞ የማስደረግና ኦሮሚያ ትቅደም የጎሣ የበላይነት ለማስፈን የሚያደርጉት በጣም ከንቱ ቅዥትና ምኞት ነው። ፈጽሞ አይሳካም።

የኦሮሞ ጎሣ ብሔረተኞች በግልጽ ሊገነዘቡት የሚያስፍልግ ዐቢይ ነገር አለ። ከሁሉ በተቀዳሚ አዲስ አበባ <u>የሸዋ ክፍለ</u> ሀገር ዋና ከተማ ናት። የወረሞ ጎሣ ብቻ ልዩ ሃብት አልነበረችም፣ አትሆንም። አዲስ አበባ (እንዶጥና) በመናገሻ አውራጅ ውስጥ የምትገኘው የኢትዩጵያ መዲና ከኦሮሞ (ጋላ) የ17ኛው ክፍለ ዘመን በፊት ከጥንት ጀምሮ ያማራ፣ የከምባታ፣ የሃድያ፣ የዳሞት፣ የጉራጌና ጋፋት ሕዝብ ምድር በሆነው ሸዋ ውስጥ ነው። ስለሆነም አዲስ አበበባ በመናገሻ አውራጃ በአራቱም ማዕዘናት መስፋት ትችላለች። አባሪ ካርታውን ይመለከቷል።
ካሳ መክፈል ያለባቸውማ በሉባ የደፈጣ ውጊያ ስልት ከኬኒያ ቦረና ጠርፍ ተነስተው በሸዋና ዙሪያ የስፈሩት የወረሞ ጎሣዎች ናቸው።
የወረሞ ጠባብ ጎሥኞች ከወያኔ ትግሬና ሻዕቢያ ጋራ ወግነው ከሐረርጌ፣ ከአሩሲ፣ ከወለጋ፣ ከደቡብና ምዕራብ ሸዋ፣ ከባሌ፣ ከኢሉባቦር ወዘተረፈ ያማራ ተወላጅ ገበሬዎችን፣ ሠራተኞችን ለይተው ጨፍጭፈዋል፣ ሃብት ንብረታቸውን ዘርፈው አፈናቅለዋል። በጎሣ ማጥፋትና ማጥራት ለተፈናቀሉትና ለሚፈናቀሉት በሚሊዎን ለሚቆጠሩት ዐማሮችስ ስለለምንድን ነው ካሳ የማይከፈለው?
በምዕራብ ሸዋ አማያ ወረዳ በቅርቡ ተፈናቅለው ወደ ጉራጌ ወገናቸው ተሰደው የሚገኙትን ዐማሮች እዚህ ላይ መጥቀስ ተገቢ ነው። ሌላው ደግሞ ከአዲስ አበባ ከተማና በዙሪያዋ የተፈናቀሉት ገበሬዎች ወረሞች ብቻ እንደሆኑ አስመስሎ ማናፈሱ ነው። በአዲስ አበባ ሆነ በደቡብና ምዕራብ ሸዋ ከሚፈናቀሉት ገበሬዎች አብዛኛዎቹ ዐማራዎች ናቸው። አፈናቃዩችም ኦሮሞ የሆኑ የታጠቁ የወያኔ ትግሬ ቅልቦችና ተላላኪዎች መሆናቸው ይታወቃል። የጊዜ ጉዳይ እንጂ ለፈጸሙት ወንጀል ለፍርድ ይቀርባሉ።

በሸዋ ይሁን በሌላው ክፍለ ሀገር ያለው ምድር የመላው ኢትዩጵያውያን እንጂ የወረሞ ጎሣ ብቻ ልዩ የግል ንብረት አይደለም። በምን ሂሳብ ነው አዲስ አበባ የኦሮሞ ብቻ ሃብትነትና ልዩ ተጠቃሚነት? ከወረሞ ይልቅ ነባር ነዋሪውና ባለርስቱማ አማራው፣ ጉራጌው፤ ጋፋት፣ ከምባታው ናቸው ናቸው። ስለሆነም የባንቱስታን የጎሣ ክልል ኦሮሚያ ተብዬውንና የኦሮሞ ብሔረተኞች ቅጥየለሽ የመስፋፋት አባዜና ክልላችን በሚሉት ውስጥ በሚኖሩት ዐማሮች ላይ የሚፈጽሙትን የጎሣ ማጽዳትና ማጥፋት ዘመቻ በአጽንኦት እንቃወማለን።

የሸዋ ሕዝብ ድርጅት (ሽሕድ )
Shoa People Organization ( SPO)
WWW.shoa.org